# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 221 ነሐሴ 3 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ትግላችን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እየተዳረሰ ነው። የሁላችንም ትኩረት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የጫነብንን ይህን አስከፊ ዘረኛ ሥርዓት ማስወገድ መሆኑን ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ይህ ሥርዓት መሠረቱ ተንዷል። በዚህ ወቅት ገለልተኛ መሆን፤ በዚህ ወቅት ግዴለሽ መሆን ከሰውነት ተርታ መውጣት ነው።

እስካሁን "እኔ ምን አገባኝ" ስትሉ ለቆያችሁ ወገኖቻችን በሙሉ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## አንጋፋዉ የህወሃት መሪና መስራች ስብሀት ነጋ ከጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ጋር ባደረገዉ ቃለምልልስ "ባጠቃላይ ሲታይ አሁን ህገ መንግስቱን ተቀብለን ነዉ የምንሄደዉ፤ ያለነዉ በስልጣን ዝዉዉር አካባአቢ ነዉ " በማለት የመለስ ዜናዊን መጨረሻ የሚጠቁም ነገር ተናገረ

ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ታምሞ የአልጋ ቁራኛ ከሆነበት ቀን ጀምሮ አንዴ አልታመመም፤ አንዴ ተሽሎታል በሌላ ግዜ ደግሞ እረፍት ላይ ነዉ እያሉ የባጥ የቆጡን ሲቀባጥሩ የከረሙት የወያኔ ባለስልጣኖች ከሰሞኑ በአንጋፋ መሪያቸዉ በስብሐት ነጋ በኩል አገራችን ኢትዮጵያ የስልጣን ዝዉዉር ላይ እንደምትገኝ በእጅ አዙር ተናግረዋል። ስብሐት ነጋ ባለፈዉ ማክሰኞ ለጀርመን ድምጽ ሬዲዮ በሰጠዉ ቃለምልልስ በረከት ስምኦንና ሽመልስ ከማል ሁለት ወር ሙሉ ሲደብቁ የከረሙትን የጠ/ሚኒስትሩን የስልጣን ሽግግር ጉዳይ ሳይወድ በግዱ ሽፍንፍን ባለ መልኩ ጠቁሞ አልፏል።

እገሌ ኖረም አልኖረ ወይም እገሊት ኖረች አልኖረች በህገመንግስቱ በሰፈረዉ መሠረት የአመራሩ አሰራር ይቀጥላል ሲል የነበረዉ ስብሀት ነጋ ይህንን ጠቋሚ ንግግር ያደረገዉ ከሰሞኑ የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ - የኢትዮጵያ ህግ መንግስት ምክትል ጠ/ሚኒስትሩ ያለዉን ስልጣን አያረጋግጥም በወኪልነት ለረጂም ግዜ መቆየት ደግሞ ችግር ያመጣልና እዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምን ይመስላል ተብሎ የተጠየቀዉን ጥያቄ ሲመልስ ነዉ።

ስብሀት ነጋ በዚህ ንግግሩ የስልጣን ሽግግሩን ብቻ ሳይሆን መለስ ዜናዊ ተሽሎት በቅርቡ ወደ መደበኛ ስራዉ ይመለሳል ሲል በረከት ስምኦን የሰጠዉን መግለጫ ዉድቅ ያደረገዉ ከመሆኑም በላይ መለስ ዜናዊ ሞቷል ተብሎ የተነገረዉ ዜና ይበልጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ አድርጓል።

በሬዲዮ ቃለምልልሱ ወቅት ከዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና ከፕሮፌሰር አድነዉ አዲስ ጋር አብሮ የቀረበዉ ስብሀት ነጋ የኢትዮጵያ ፓርላማ ጠ/ሚኒስትሩን መሾም ብቻ ሳይሆን ካሰኘዉ በየወሩ መቀያየርም ይችላል (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በአንዱአለም አራጌና በእስክንድር ነጋ ላይ የተላለፈዉን የፍርደ ቤት ዉሳኔ አስመልቶ አንድነት ፓርቲ ያወጣዉን መግለጨ ህገ ወጥ ነዉ ሲል የፓርቲዉን ከፍተኛ ባለስልጣናት አስጠነቀቀ

አንድነት ፓርቲ በአንዱአለም አራጌ፤ በእስክንድር ነጋና በሌሎችም ተከሳሾች ላይ የፌፌራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈዉን ዉሳኔ በማዉገዙ ፍርድ ቤቱ የፓርቲዉን ከፍተኛ ባለስልጣናት አስጠርቶ ተግሳጽና ማስጠንቀቂያ እንደሰጠ ሁኔታዉን በቅርብ የተከታተለዉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ገለጸ። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የፖለቲካ መሳሪያ የሆነዉ የፌዴራሉ ፍርድ ቤት "የፓርቲዉ መግለጫ የፍርድ ቤቱን ነፃነት የሚጋፋ ብቻ ሳይሆን አደጋ ላይ የሚጥል ነዉ" ብሎ ሲናገር ችሎቱ ዉስጥ የነበረዉን አብዛኛዉ ሰዉ እንደሳቀ ምንጫችን አክሎ ገልጿል። ሊገፋ ቀርቶ ለእይታም የሚበቃ ነፃነት የሌለዉና የወያኔ ስርአት እስረኛ የሆነዉ ፍርድ ቤት ስለ ነፃነት ማዉራቱ በአስተሳሰብ ደረጃ "አያ ጅቦ ሰታመካኝ ብላኝ" ካለችዉ እንስሳ ምንም እንደማይሻል በግልጽ ያሳያል ሲሉ የፍርድ ቤቱን ዉሎ በቅርብ የተከታተሉ ሁሉ በአጽንኦት ተናግረዋል።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአንድነት ፓርቲ መሪዎችን ፍርድ ቤት አስጠርቶ ፓርቲዉ የፍርድ ቤቱን ዉሳኔ አስመልክቶ ያወጣዉ መግለጫ በከፍተኛ ደረጃ የሚያስቀጣ ጥፋት መሆኑን ከገለጸ በኋላ ፓርቲዉ ለመድበለ ፓርቲ ስርአት ግንባታ የሚያደርገዉን አስተቃጽኦ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ይህንን ጥፋት በማስጠንቀቂያ እንደሚያልፈዉ ጨምሮ ገልጿል። የፓርቲዉ ከፍተኛ አመራር አባል በሆነዉ በአንዱአለም አራጌ ላይ የግፍ ፍርድ የፈረደዉ ፍርፍ ቤት አንድነት ፓርቲ ለመድበለ ፓርቲ ስርአት ግንባታ ስለሚያደርገዉ አስተዋጽኦ መናገሩ ኢትዮጵያ ዉስጥ የመድበለ ፓርቲ ስርአት ያለ ለማስመሰል የተነገረ ተራ የመንደር ወሬ ከመሆኑ ዉጭ ምንም ቁም ነገር ያላዘለ ባዶ አባባል መሆኑን አንዳንድ የስርአቱ ደጋፊዎች ጭምር በይፋ በመናገር ላይ ናቸዉ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## በመለስ ዜናዊ አለመኖር የተነሳ ሊፈጠር የሚችለዉን የስልጣን ክፍተት አስመልክቶ ወያኔ ጦር ዉስጥ በስርዐቱ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል ከፈተኛ ፍጥጫ ተፈጠረ

ካለፈዉ ሰኔ ወር አጋማሽ ጀምሮ ደብዛዉ የጠፋዉን መለስ ዜናዊን ማን ይተካዋል የሚለዉ ጥያቄ በወያኔ ሠራዊት ዉስጥ ተነስቶ በስርአቱ ተጠቃሚ በሆኑትና ለዉጥ ፈላጊ በሆኑት የሠራዊቱ አባላት መካከል የሞቀ ክርክር እየተነሳ በየቦታዉ ሠራዊቱን ለሁለት የከፈለዉ መሆኑን ከወያኔ ጦር እየከዱ ከወገን ነጻ አዉጭ ሀይሎች ጋር የሚቀላቀሉ ብዛት ያላቸዉ የሠራዊቱ አባላት አጋለጡ። ወያኔ ሠራዊቱን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት እያለ ይጥራዉ እንጂ በትግራይ መኮንኖች ብቻ የሚመራዉ የወያኔ ጦር አንድም ቀን የኢትዮጵያዊነት ባህሪይ ታይቶበት አያዉቅም ያሉት አነዚህ የሰራዊቱ አባላት በጦሩ ዉስጥ የሚታየዉ መከፋፈል የከፋ መሆኑንና የአሁኑ ደግሞ ጭራሽ አደገኛ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደነዚህ የወያኔን ጦር ከድተዉ እንደመጡት ወታደሮች አባባል ወያኔ በሠራዊቱ መካከል የገነባዉ የዘር ግድግዳ አገሪቱ ዉስጥ በሌላዉ ዘርፍ ከሚታየዉ ዘረኝነት የባሰ መሆኑንና በሠራዊቱ መካከል እርስ በእርስ መነጋገርና መወያየት ቀርቶ ደጋግሞ ሠላምታ መለዋወጥም እንደማይፈቀድ ታዉቋል።አብዘኛዉ የሠራዊቱ አባል ለዉጥ ፈላጊ ቢሆንም ስለለዉጥ ማዉራት ቀርቶ ያስባል ተብሎ የተጠረጠረ ወታደር የጭካኔ እርምጃ እንደሚወሰድበት እነዚሁ ወያኔን ከድተዉ የመጡ ወታደሮች ተናግረዋል። ወታደሮቹ አገር ቤት ካለዉ የሠራዊቱ አባላት ጋር የጠበቀ ግኙኙነት እንዳላቸዉና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ግዜ ሁሉ የትግል ጥሪ አንደሚያደርጉላቸዉም ጨምረዉ ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በሙስሊሞች ላይ እየደረሰ ያለ ወከባ ቀጥሏል፤ ሕዝቡ ግን መስቀል አደባባይ እንገናኝ እያለ ነው

በሙስሊስ ወንድሞችና እህቶች ላይ የሚደርሰው ወከባ፣ እስርና እንግልት በመላው አገሪቱ ውስጥ የተስፋፋ መሆኑን እየደረሱን ያሉ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

ለምሳሌ በቄለም ወለጋ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች በአወሊያ ከተቋቋመው ኮሚቴ ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል ሰዎች ለእስር እየተዳረጉ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች አመለከቱ፡፡ በዳሌዋበራ ሐዋ ገላንና ገወቄሌ ወረዳዎች በሚኖሩ ዑለሞችና ኡስታዞች ላይም ማስፈራሪያና ወከባው ተጠናክሯል፡፡

በበራዩ አካባቢ የሚገኙ ሙስሊሞችን መንግስት በየቤቱ እየዞረ ኮሚቴዉን ተቃዉማችሁ ሰልፍ ዉጡ በማለት እያስገደደ መሆኑን የሙስሊም ጉዳዮችን የሚከታተሉ ድረገጾች አስታወቁ።

በመላው አገሪቱ ማለት ይቻላል "የሙስሊሙን እንቅስቃሴ በመቃወም ሰልፍ የማትወጡ ከሆነ እናንተ ራሳችሁ አክራሪዎችና ፀረ-ልማቶች ተብላችሁ ትታሰራላችሁ" በማለት የወያኔ ካድሬዎች ሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን እያስፈራሩ ይገኛሉ።

እንዲህ በሙስሊሞች ላይ የሚደርሰው ወከባ ተጠናክሮ ባለበት ሰዓት በሌላ በኩል ደግሞ በሽምግልና ስም ትግሉን ለማቀዝቀስ ወያኔ የሚያደርገው ጥረት ቀጥሏል። የሙስሊም መሪዎችን ለማስፈታት በሚደረገው የሽምግልና ጥረት ውስጥ አንዳንድ የሃገር ሽማግሌዎችና ምሁራን ያሉበት ቢሆንም ወያኔ እንደለመደው ሽምግናውን ለራሱ ጥቅም እንደማይጠቀምበት ማረጋገጫ የለም የሚሉ ወገኖች በርካቶች ናቸው። ወያኔ ውጥረት ውስጥ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት አባላትን ያቀፈው ነጻ የኢትዮጵያ ሰራዊት ንቅናቄ ለአንድነት፣ ለፍትህ፣ ለነጻነት ( ነኢሰን ) የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚያደርገው የነጻነት ትግል ጎን ለመሰለፍ ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ሃምሌ 2004 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ይፋ አደረገ

ንቅናቄው የኢትዮጵያ ህዝብ ለአንድነት፣ ለፍትህ፣ ለነጻነት ከሚያደርገው ትግል ጎን ለመሰለፍ የጀመረውን እንቅስቃሴ ማጠናቀቁን ይፋ ባደረገበት የማእከላዊው ኮሚቴ መግለጫ እንዳለው የኢትዮጵያ የመከላከያ ፣የፖሊስና የደህንነት ሃይል በጥቂት የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች እግር ተወርች ታስሮ የመጨቆኛ መሳሪያ መሆኑን በማመንና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው መከራ በሰራዊቱ ላይ ይበልጥ በከፋ መልኩ እየተፈጸመ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ህዝቡ ይህንን ግፈኛና ዘረኛ ስርዓት ለማስወገድ ከሚያካሂደው ትግል ጎን ተሰልፏል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይል በተለያዩ ወቅቶች ዳር ድንበር ከማስከበር አልፎ ከህዝብ ጎን በመቆም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## “ምን አገባኝ” ማለት ለጠላት ማጎብደድ ነው

ከጀርመን ዘረኛ ናዚዎች ጭፍጨፋ ከሞት ከተረፉ ብዙ ዓመታት በኋላ የኖቤል የሰላም ሽልማት ተሸላሚ የሆኑት ኤል ዊይሰል እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር በአፕሪል 12 1999 የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተንና ባለቤታቸው ሂላሪ ክሊንተን በተገኙበት ጉባኤ ላይ በዓለም ታላላቅ ንግግሮች ከሚባሉት አንዱን አደረጉ። የንግግራቸው ጭብጥ “እኔን ምን አገባኝ” እያሉ ከትግል መሸሽ ስለሚያስከትለው አደጋ ነበር።

ኤሊ ዊይሰል በዚህ ንግግራቸው ካሉት ጥቂት ብቻ እንጥቀስ

*በብርሃንና በጨለማ፤ በምሽትና በቀን፤ በወንጀልና በቅጣት፤ በጭካኔና በፍቅር፤ በጥሩና በመጥፎ መካከል ግድ የሌለው ሰው መሆን ተፈጥሮዓዊ አይደለም”። ጎረቤቶቻቸው ሲበደሉ፣ ሲገረፉና ሲደገሉ እያዩና እየሰሙ ራታቸውን በልተው፤ ወይን ተጎንጭተው በሰላም እንቅልፋቸውን የሚተኙ ሰዎች ጤነኞች ሰዎች አይደሉም።*

*እርግጥ ነው በሌላ ሰው ስቃይ ውስጥ ጣልቃ መግባት በራስ ላይ ስቃይን መጋበዝ ስለሚሆን “ምን አገባኝ” ቀላል መሸሻ ነው። ሆኖም ግን ይህ “ምና አገባኝ” ነው እኛን ከሰውነት ተርታ የሚያወጣን። ..... “ምን አገባኝ” ከግልጽ ጥላቻ የከፋ ነው።*

ግዴለሽነት ፈጽሞ ሰውኛ ነገር አይደለም።

የኤል ዊይሰል ንግግር ያተኮረው በጀርመን ናዚ ወቅት ብዙዎች ባሳዩት ግዴለሽነት የደረሰውን ጥፋት ለማመልከት ቢሆንም ከዚያ ጊዜ ወዲህ “ምን አገባኝ” የአምባገነኖች ምሽግ ሆኖ ቆይቷል።

እኛም አገር ውስጥ “እኔን ምን አገባኝ” የሚሉ ብዙ ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ “ጭብጥ በማይሞሉ” ጥቂት ሰዎች ታግዞ እንዲህ እንዳሻው ባልፈነጨብንም ነበር። የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ጉልበት የሰጠው የብዙ ሰዎች “እኔን ምን አገባኝ” የሚለው ሽሽት ነው።

- ወገኖቻችን ሲረገጡ፣ ሲሰደዱ፣ ሲታሰሩ፣ ሲደበደቡ፣ ሲጋዙ፣ሲሰደቡ፣ ሲገደሉ እያየን፤ መናገርም መስማትም ወንጀል ሆኖ ሲያስቀጣ እየታዘብን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?
- ገዢዎችና ምስለኔዎቻቸው በህንፃ ላይ ህንፃ፤ በሃብት ላይ ሃብት ሲጨምሩ እያየን እኛ የእለት እንጀራ ማጣታችንን እንዴት ተቀብለን እንኖራለን?
- ለጋ ኮረዳዎች ለቤተሰቦቻቸው ስንቅና ልብስ የሚሆን ጥሪት ለማፍራት ለአረብ አገራት ግርድና ሲሸቀዳደሙ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ልጃገረዶች ለግርድና ወረፋ ሲጠብቁ እያየን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?
- ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች ቁራሽ መሬት አጥተው ለቀን ሠራተኝነት ደቡብ አፍሪቃ ድረስ በእግራቸው ለመሄድ ከሠፈራቸው ነቅለው ሲነሱ ለአረብና ቻይኛ ቱጃሮች ከመቶ ጋሻ በላይ ለም መሬት ሲሰጥ እያየን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?
- ገዳሞቻችን እና መስጊዶቻችን ሲደፈሩ እንዴት ዝም እንላለን?
- ሰላማዊ ዜጎች “ሽብርተኛ” እየተባሉ ሲፈረድባቸው እያየን እና እየሰማን እንደምን ዝም እንላለን?
- ጥቂቶች በዘራቸው እየተመረጡ ሲሾሙና ሲሸለሙ፤ ብዙሃን ደግሞ በዘራቸው ምክንያት ሲሰደቡ፣ ሲዋረዱ እና ሲበደሉ እያየን እንዴት ዝም እንላለን?
- የመንግሥት ስልጣን እና ሃብት በዘር መስፈርት ሲታደል እያየን እንዴት አስችሎን ዝምታን እንመርጣለን?
- ጥቂቶች ብዙሃንን ባርያ አድርገው ሲገዙ እያየን ዝም ስንል እኛ ራሳችን ለባርነት መስማማታችን እንደሆነ እንዴት ይጠፋናል?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ ግዴለሽነት ማብቃት አለበት ይላል።

ትግላችን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እየተዳረሰ ነው። የሁላችንም ትኩረት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የጫነብንን ይህን አስከፊ ዘረኛ ሥርዓት ማስወገድ መሆኑን ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ይህ ሥርዓት መሠረቱ ተንዷል። በዚህ ወቅት ገለልተኛ መሆን፤ በዚህ ወቅት ግዴለሽ መሆን ከሰውነት ተርታ መውጣት ነው።

እስካሁን “እኔ ምን አገባኝ” ስትሉ ለቆያችሁ ወገኖቻችን በሙሉ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል።

የነፃነት ትግልን “በምን አገባኝ” መሸሽ ለጠላት ከመገበር ተለይቶ አይታይም። ስለሆነም ሳይዉል ሳያድር ትግላችንን ተቀላቀሉ!!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አንጋፋዉ የህወሃት መሪና መስራች ስብሀት ነጋ ከጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ጋር ባደረገዉ ቃለ ምልልስ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሲል ከመደመጡም በላይ ለተጠየቀዉ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ከመስጠት ይልቅ ያንን የተለመደ ዘረኛ የፖለቲካ ጅራፉን እንዳጮኸ የሦስትዮሹ ዉይይት ተጠናቅቋል።

ስብሀት ነጋ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዋናዉ የመሪነት ቦታ ለተቀሩት ሦስቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች የሚዳረስበት ሁኔታ ይኖራል ወይስ ዋናዉ ቁንጮ መሪ ህወሀት ብቻ ነዉ የመሪነቱን ቦታ እንደያዘ የሚቀጥለዉ ብሎ ለጠየቀዉ ጥያቄ ሲመልስ ከጥያቄዉ ጋር ፍጹም የማይገናኝ መልስ በመስጠትና አንዳንዴም ጠያቂዉ ላይ “አባባልህ ልክ አይደለም” የሚል ክስ በመሰንዘር ኢትዮጵያ ዉስጥ ዋናዉ የመሪነት ቦታ ከህወሀት እጅ በፍጹም እንደማይወጣ ግልጽ አድርጓል።

## የፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በአንዱአለም አራጌና በእስክንድር ነጋ ላይ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ዳግም ላይመለስ ጠፍቷል እየተባለ በሚነገርበት ወቅት የወያኔ አባላት ምን ያክል ከመለስ ዜናዊ የከፉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማሳየት ከግዜ ጋር እሽቅድምድም የገቡ ይመስላል ስትል አንዲት ችሎቱ ዉስት ቁጭ ብላ የፍርድ ቤቱን ዉሳኔ የተከታተለች የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪ ለግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ በሰጠችዉ ቃለ ምልልስ ተናግራለች።የህግ ተማሪዋ ከዚህ ጋር በማያያዝ ይህ የወያኔዎች ድንብርብሩ የወጣ ሩጫ የሚያሳየን እነዚህ ዘረኞች ህዝባዊዉን ትግል ለመግታትና ብሎም ለማኮላሸት የማያደርጉት ነገር እንደሌለ ነዉ፡ ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያዉያን በአጭር ታጥቀን ወያኔን በፍጥነት የማናስወግደዉ ከሆነ መጪዉ ግዜ ከቀድሞዉ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ተናግራለች።

## በመለስ ዜናዊ አለመኖር የተነሳ ሊፈጠር የሚችለዉን የስልጣን ክፍተት አስመልክቶ ወያኔ ጦር ዉስጥ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መለስ ዜናዊ ከነስርአቱ ይጥፋ በሚሉና ከህወሀት ዉጭ ማንም አይገዛንም በሚሉ ትግርኛ ተናጋሪ የሠራዊቱ አባላት መካከል ለወራት የዘለቀዉ ፍጥጫ ሰሞኑን የመለስ ዜናዊን ሞተ የሚለዉን ዜና አስታክኮ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ ታዉቋል። ከወያኔ ጦር እየከዱ ከሚመጡት ወታደሮች በተገኘዉ መረጃ መሠረት ወያኔዎች ከትግራይ ዉጭ የመጡትን የሠራዊቱ አባላት ስለማያምኗቸዉ ከግዳጅ ዉጭ መሳሪያ በእጃቸዉ እንዲነኩ ስለማይፈቅዱላቸዉ ነዉ እንጂ ወያኔ እስከዛሬ እንደማይቆይ ብዙዎች በእርግጠኝነት የሚናገሩት ሀቅ ነዉ። በአሁኑ ወቅት ዘረኝነትን ማዉገዝ በጦሩ ዉስጥ የተለመደ ተግባር እየሆነ መምጣቱ የወያኔን ባለስልጣኖች ክፉኛ ያስደነገጣቸዉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዉ የሠራዊቱ አባል ትግርኛ በሚናገሩ ሰዎች ብቻ መታዘዝ እንደሰለቸዉ ለማወቅ ተችሏል።

## በሙስሊሞች ላይ እየደረሰ ያለ ወከባ ቀጥሏል፤ ሕዝቡ ግን መስቀል አደባባይ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በሚገባበት ጊዜ መሪዎችን ሰብስቦ ካሰረ በኋላ በሽምግልና ስም ነገሩን በማጓተት ጊዜ የሚገዛ፤ የትግሉንም መንፈስ የሚያቀዘቅዝ መሆኑ ከምርጫ97 ጀምሮ የሚታወቅ ጉዳይ በመሆኑ የሽምግልና ጥረትም በጥርጣሬ ለመመልከት ምክንያት ሆኗል ይላሉ እነዚህ ወገኖች።

ወያኔ እስካልተገደ ድረስ የሙስሊሙ ጥያቄ ምላሽ አያገኝም የሚሉ ድምጾች ከየአቅጣው እየመጡ እየመጡ ነው። ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ትግላችንን ከመስጊድ ወደ አደባባይ እናወጣዋለን እያሉ ነው። እነዚህ ወጣቶች በመጅሊስ እና በዋልድባ ጉዳዮች ሳንወሰን ትግላችን የክፋቶች ሁሉ ምንጭ በሆነው ወያኔ ላይ ማነጣጠር ይገባናል እያሉ ነው። በዚህም ምክንያት “ኑ መስቀል አደባባይ እንገናኝ!!!” የሚሉ ጥሪዎች በፌስ ቡክና በሞባይል አጭር መልዕክቶች መተላለፍ መጀመረራቸው ባደረግነው ዳሰሳ አረጋግጠናል።

# ከጥሩ ወደ ታላቅ

## አንዳንድ ድርጅቶች ታላቅ ለውጥ ማምጣት ሲችሉ ሌሎቹ የሚያቅታቸው ለምንድነው?

### በንቅናቄዓችን ትምህርትና ሥልጠና የተዘጋጀ

**መቅደም**

የንቅናቄዓችን የሥራ አፈፃፀም ምን ይመስላል?

ግንቦት 7 የአራት ዓመታት ጨቅላ ድርጅት ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ራሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስተዋወቅን ጨምሮ በትብብር፣ በሕዝብ ግኑንኘትና በአባላት ምልመላ ረገድ ያከናወናቸው ተግባራት በርካታ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በአገር ቤትም በውጭ አገራትም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያከናውናቸው ተግባራት ወያኔን እንቅልፍ ነስተዋል። እነዚህ እና የመሳሰሉት በዝርዝር ከተጤኑ ግንቦት 7 "ጥሩ" እየሠራ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም ደግሞ የግንቦት 7ን የሥራ አፈፃፀም ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር ካወዳደርነው ምናልባትም "በጣም ጥሩ" የሚል ውጤት ለመስጠት ይዳዳን ይሆናል።

ለመሆኑ "ጥሩ" የሚባል ውጤት ማግኘት የሚያረካ ነው? በጭራሽ። እንኳንስ ወያኔን የመሰለ መሠሪ ጠላትን ለማስወገድ ቀርቶ በኳስ ጨዋታ እንኳን "ጥሩ መጫወት" ዋንጫ አያስገኝም። ዋንጫ ለማግኘት ከሁሉም ተጋጣሚዎች የተሻለ መጫወት ይገባል።

ታላቅ ውጤት ለማግኘት ያቀዱ ድርጅቶች ራሳቸው ታላቅ መሆን ይገባቸል። ጥሩ የሚሠሩ ድርጅቶች በጥሩነታቸው ብቻ ከቀጠሉ ለታላቅ ውጤት አይበቁም። ታላቅ ግብ አስቀምጦ "ጥሩ" በሚያስብል ደረጃ መሥራት ከመጥፎ የሥራ ውጤት የተሻለ አይደለም።

ስለሆነም እስካሁን በሠራነው ምንም የምንመካበት የለም። ንቅናቄዓችን ለታላቅ ግብ አልሞ የተነሳ በመሆኑ ራሱን ከጥሩነት ወደ ታላቅነት (from Good to Great) መቀየር አለበት። ትልቁ ችግር "ምን ብናደርግ ነው ንቅናቄዓችንን ከጥሩነት ወደ ታላቅነት የምንቀይረው?" የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው።

ጂን ኮሊን እና ባልደረቦቹ ታላላቅ የተባሉ ኩባንያዎችን አጥንተው ያዘጋጁትና በአመራር ስልጠና በከፍተኛ ሁኔታ ተነባቢ የሆነው "Good to Great: Why Some Companies Make the Leap .... and Others Not" የተሰኘውን መጽሃፍ አሳጥረን ለአባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ለአባቢያን ሁሉ ማቅረብ ወሰንን። አንባቢያን ይህን ጽሁፍ በጥሞና አንብበው ይወያዩበታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ጽሁፍ መጽሃፉ አጥሮ ከመቅረቡ በስተቀር የእኛ አስተያየት አልታከለበትም። ስለሆነም ከዚህ በታች የሚናገረው የመጽሃፉ ደራሲ ነው።

**መግቢያ**

- እንዴት ነው ብዙዎች ጥሩ ድርጅቶች እያደር ሲደክሙ አንዳንዶች ለረዥም ጊዜ የላቀ ውጤትን እያስመዘገቡ ሊቆዩ የሚችሉት?
- ጥሩ ወይም በመካከለኛ ደረጃ ላይ ያሉ ድርጅቶች ወደላቀ ውጤት አስመዝጋቢነት እንዲያድጉ ማድረግ ይቻላልን?
- አንድ በመጥፎ ሁኔታ ላይ ያለ ድርጅትን የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ወደሚችል ድርጅትነት መቀየር ይቻላልን?

እነዚህ ጥያቄዎች ለዓመታት በአዕምሮዓችን ውስጥ ሲመላለሱ የቆዩ ናቸው።

ወደ ጎታታነትና ዘገምተኝነት የሚስባቸውን ኃይል ተቋቁመው ለረዥም ጊዜ ኮከብ ሆነው የቆዩ ድርጅቶች አሉ? ካሉ፤ የእነዚህ ድርጅቶች የተለዩ ባህሪያት ምንድናቸው? እነዚህ ድርጅቶች ከጥሩ ወደ ታላቅነት (from Good to Great) እንዲሸጋገሩ የረዳቸው ምስጢር ምንድነው?

ይህንን ምስጢር ለመፍታት ተነሳን ለአስራ አምስት ዓመታት የላቁ ውጤቶችን ሲያስመዘግቡ የነበሩ ድርጅቶችን (ኩባንያዎችን) መረጥን። ለረዥም ጊዜ የላቀ ውጤት ሲያስመዘግቡ የቆዩ ድርጅቶችን ከመረጥን በኋላ በተለያዩ መንገዶች ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በማወዳደር ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ጣርን።

- ምንድነው እነዚህን ድርጅቶች ልዩ ያደረጋቸው?
- ከሌሎቹ ድርጅቶች በተለየ ሁኔታ እነዚህ ድርጅቶች ለዓመታት የላቀ ውጤት ሊያስመዘግቡ ያስቻላቸው ምስጢር ምንድነው?

ሃያ ሁለት ድርጅቶችን ለአምስት ዓመታት በጥልቀት አጠናን። በሺዎች የሚቆጠሩ ቃለመጠይቆችን አደረግን። መዛግብትን መረመርን። ከብዙ ልፋት በኋላ አንዳንድ ድርጅቶች የላቀ ውጤት ማስመዝገብ የሚችሉበት ምስጢር አገኘን። ይህ መጽሃፍ የዚህ ጥናታችን ውጤት ነው።

የጥናታችን ውጤት ብዙዎችን ማስገረሙ አይቀረም። ብዙ ያልጠበቅናቸው ውጤቶችን በማግኘታችን ለእኛን ለራሳችን አስደናቂ ውጤት ነው። የኛ የጥናት ውጤት የማኔጅመንትን ስትራቴጂን ልዩ ልዩ ክፍሎችን ነክቷል።

የጥናታችንን ውጤት በሚከተሉት ጥቂት መስመሮች ማጠቃለል ይቻላል።

1. አምስተኛው እርከን አመራር (Level 5 Leadership)። የላቀ ውጤት ማስመዝገብ የሚችል ድርጅት ለመፍጠር በአምስተኛው እርከን ላይ የሚገኝ አመራር ያስፈልጋል።
2. የጃርቷን ተምሳሌት መከተል (The Hedgehog Concept):; ከጥሩ ወደ ታላቅነት ለመሸጋገር "መርገምተ- ብቃት" መሸጋገር እና በአንድ ዋነኛ ሥራ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል።
3. ጠንካራ ሥነሥርዓት ያለበት ድርጅታዊ ባህል ( A Culture of Discipline። ከጥሩ ወደ ታላቅነት ለመሸጋገር ስነምግባርን ከጠንካራ ድርጅታዊ ዲሲፕሊን ጋር ማዋሃድ ያስፈልጋል። ዲሲፕሊን ሳይኖር ታላቅነት የለም።
4. የቴክኖሎጂ አራማጆች (Technology Accelerators)። ከጥሩ-ወደ-ታላቅነት የሚሸጋገሩ ድርጅቶች ለቴክኖሎጂ ያላቸው አመለካከት የተለየ ነው።
5. መዘውሩ እና መሰናከሉ (The Flywheel and the Doom Loop)። ከባድ የሚባሉ ለውጦች አንዴ ከተጀመሩ በኋላ እንደ መዘውር ቀስበቀስ ፍጥነታቸው እየጨመረ መሄድ ይኖርባቸዋል። አንድ ድርጅት በአንዴ ታላቅ አይሆንም። እንደ መሰናከል ሩጫ በየጊዜው እየተዘለለ የረዥም ጊዜ እድገት ማስመዝገብ አይቻልም።

**ምዕራፍ I: ጥሩ የታላቅነት ጠላት ነው /Good is the Enemy of Great/**

ጥሩ ድርጅት መሆን "ታላቅ" የመሆንን መንገድ ይዘጋል። ስለዚህም ጥሩ የታላቅነት ጠላት ነው። ብዙ ጥሩ ድርጅቶች ያሉን መሆኑ ታላላቅ ድርጅቶችን እንዳናገኝ አድርጎናል። ልዩ ውጤት የሚያስመዘግቡ ት/ቤቶች የአለመኖራቸው ዋነኛ ምክንያት ደህና ውጤት የሚያስመዘግቡ በርካታ ት/ቤቶች ስላሉን ነው። የጥሩ መንግሥት መኖርም እጅግ በጣም ጥሩ መንግሥት እንዳይኖን ምክንያት ሊሆን ይችላል። በ C የሚደሰት ተማሪ A እንደናፈቀው ይኖራል።

ብዙ ድርጅቶችም የላቀ የውጤት ደረጃ ላይ የማይደርሱት በሚያገኙት መካከለኛ ውጤት ስለሚረኩ ሊሆን ይችላል።

ይህ መጽሃፍ በተወሰነ ኩባንያዎችና ድርጅቶች የሥራ ውጤት ላይ የተደረገ ምርምር ውጤት ቢሆንም ጠቃሚነቱ ለእነዚህ ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች ብቻ አይደለም። ይህ መጽሃፍ ጠቃሚነቱ ለሁሉም ኩባንያዎች እና ድርጅቶች ነው። ይህ መጽሃፍ የተፃፈው የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ለሚፈልጉ ድርጅቶች በሙሉ ነው። እንዲያውም ብዙዎቹ ግኝቶች ለድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ለግለሰብም ጭምር ሊውሉ የሚችሉ ናቸው።

ዋነኛው የምርምሩ መንገድ ከጥሩ ወደ ታላቅነት የተሸጋገሩ ድርጅቶችን በማወዳደር የጋራ ባህሪያትን መፈለግ ነበር። እነዚህን ድርጅቶች ምንድነው ልዩ ያደረጋቸው? የሚለው ጥያቄው የምርምሩ መሪ ጥያቄ የነበረ ሲሆን "የማይጮሁ ውሾችን" መፈለግም ሌላው ሥራ ነበር። "የማይጮሁ ውሾች" የተባሉት ለመጥፎ የሥራ ውጤት ምክንያት የሚመስሉ ግን ያልሆኑ ነገሮችን ነው።

**ምዕራፍ II: አምስተኛ እርከን አመራር /Level 5 Leadership/**

የዚህ ምርምር አንዱ ትልቁ ውጤት የመሪዎች ብቃት የድርጅትን ውጤታማነት የሚወስን መሆኑ በንድፈሃሳብ ደረጃ ሳይሆን በተግባር መረጋገጡ ነው። ለታላቅነት የሚፈለገው አምስተኛ እርከን ላይ ያለው የአመራር ዓይነት ነው።

አምስተኛው እርከን ላይ የሚገኙ መሪዎች ስለ ራሳቸው ያላቸው ግምት ከራሳቸው ግለስብዕና አንስተው ከድርጅቱ ጋር ማዋሃድ የቻሉ ናቸው። እነዚህ መሪዎች እንደ ማንኛውም ሰው የግል ፍላጎቶችና የተለያዩ "ጥማቶች" አሉዋቸው። እንዲያውም እነዚህ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች የበለጠ ለብዙ ነገሮች የጋለ ፍላጎትና ጉጉት አላቸው። ሆኖም ግን "ጥማቶቻቸውና' ጉጉቶቻቸው ከድርጅቶቻቸው ውጤታማነት ጋር የተያያዙ ናቸው።

አምስቱ የመሪነት እርከኖች የሚከተሉት ናቸው።

**እርከን አምስት: ሥራ አስፈፃሚ (Executive )**

- ትህትናንና ሙያዊ ብቃትን በማዳቀል ድርጅቱን ለዘላቂ ታላቅነት መምራት የሚችል

**እርከን አራት: ውጤታማ መሪ (Effective Leader)**

- የድርጅቱን ራዕይ በትጋት የሚከተል፤ ለከፍተኛ ጥራት የሚተጋ መሪ

**እርከን ሶስት: ብቁ ሥራ አስኪያጅ (Competent Manager)**

- ሰዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን አስቀድሞ ለታሰበባቸው ግቦች ስሉጥ እና ፍሬዓማ በሆነ መንገድ ማደላደል የሚችል መሪ

**እርከን ሁለት: አስተዎፅዖው የጎላ የቡድን አባል (Contributing Team Member)**

- የግል ችሎታዎቹን ለቡድን የሚያውልና ከሌሎች የቡድኑ አባላት ጋር ተግባብቶ መሥራት የሚችል

**እርከን አንድ: ከፍተኛ ችሎታ ያለው ግለሰብ (Highly Capable Individual)**

- ችሎታዎቹን፣ እውቀቱንና ተሰጥዖዎቹን ተጠቅሞ ለመልካም ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማበርከት የሚችል ግለሰብ

(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## መለስ ዜናዊ ኖረም አልኖረ እሱ የገነባዉ ዘረኛ ስርዐት በመፈራረስ ላይ መሆኑን የሚጠቁሙ ብዙ ምልክቶች ኢትዮጵያ ዉስጥ በመታየት ላይ ናቸዉ ተባለ

መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ላለፉት ሃያ አንድ አመታት ሲገነቡ የከረሙት ዘረኛና ፀረ ህዝብ ስርዐት ከስርዐቱ ከራሱ በመነጩ ዉስጣዊ ቅራኔዎች የተነሳ በመፈረካከስ ላይ መሆኑን በደቡብ ክልል ምክር ቤት ዉስጥ የተፈጠረዉ መከፋፈል፤ የወጣትና የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት መሪዎች አገር እየለቀቁ ለትግል መሰደድና በወያኔ ጦር ዉስጥ እራሳቸዉን በህቡዕ እያደራጁ ጫካ የሚገቡ ወታደሮች ቁጥር ከግዜ ወደ ግዜ እየተበራከተ መምጣት አመልካች ነዉ ሲሉ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ምዕራባዉያን የፖለቲካ ተኝታኞች ተናገሩ። እንደነዚህ ለግዜዉ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ የፖለቲካ ተንተኞች እምነት የወያኔ ስርዐት የህዝብን ጥያቄ ተቀብሎ ማስተናገድ ባለመፈለጉ መዉደቂያዉ አፋፍ ላይ የደረሰ መሆኑንና ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያ ዉስጥ በህዝብ ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ መንግስት ቢፈጠር የአፍሪካን ቀንድ ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል የፖለቲካ ቀዉስ ሊፈጠር ይችላል ባይ ናቸዉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ዉስጥ በየክልሉ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች የሚልኩልን የተለያዩ ዘገባዎች ይህንኑ የምዕራባዉያን ድፕሎማቶች ትንታኔን የሚደግፉ ሆነዉ ተገኝተዋል። ለምሳሌ ባለፈዉ ሳምንት በደቡብ ክልል ዉስጥ በክልሉ ምክር ቤት አፈጉባኤና በደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት ተብዬዉ ሽፈራዉ ሽጉጤ መካከል የተከሰተዉ የፖለቲካ ፍጥጫና ይህንኑ ተከትሎ የተፈጠረዉ የምክር ቤቱ መከፋፈል የስርአቱን መፈራረስ ብቻ ሳይሆን በራሱ መቆም የማይችል ስርአት መሆኑን ያመለክታል የሚሉ ብዙዎች ናቸዉ።

በተለይ ደቡብ ክልል ሲዳማ ዞን ዉስጥ ለሲዳማ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን ለወያኔ ፍርፋሪ ያደረዉ ሽፈራዉ ሽጉጤ የወረዳዉን ከፍተኛ ባለስልጣናት ሰብስቦ ህዝብን የማሳመን በቂ ስራ አልሰራችሁምና በዚህ ተጠያቂዎች ናችሁ ብሎ ወቀሳዉን ሲጀምር የክልሉ ምክር ቤት አፈጉባኤና ሌሎችም የምክር ቤቱ አባላት ተራ በተራ እየተነሱ "ጥያቄው የህዝብ ጥያቄ ነው፣ እኛ ከህዝብ ጋር የምንጣላበት ነገር አይኖርም ፣ ህዝቡን መብታችሁን አታስከብሩ ብለን አንቀሰቅስም" በማለት የደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት ተብዬዉ ሽፈራዉ ሽጉጤ የህዝብን ጥያቄና ችግር የማያዉቅ በጥቅም የተገዛ ተራ ፖለቲከኛ መሆኑንና ክልሉ ከአሁን በኋላ በእጅ አዙር እየተገዘ እንደማይቀጥል አረጋግጠዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአገሪቱ ዉስጥ የተስፋፋዉ የአስተዳደር ብልሹነትና በጦሩ ዉስጥ የሚታየዉ ያገጠጠ የዘረኝነት ስርዐት ያንገፈገፋቸዉ በወያኔ ሰራዊት ዉስጥ የሚገኙና ከተለያዩ አገሪቱ ክልሎች የመጡ የሠራዊቱ አባላት እራሳቸዉን በህቡዕ አደራጅተዉ ከሠራዊቱ በመገለል በረሃ እየገቡ የወያኔን ስርዐት መፋለም የጀመሩ መሆናቸዉ የስርአቱን መዉደቅ በግልጽ የሚያሳይ መሆኑ እየተነገረ ነዉ። የወያኔን ትዕዛዝ ተቀብለዉ በገዛ ወገኖቻቸዉ ላይ ከመተኮስ አንዱኑ ትዕዛዝ ሰጪዉን ወያኔን እራሱን ማጥፋት ይሻላል ብለዉ ጫካ የገቡት ወታደሮች እንደሚናገሩት በጦሩ ዉስጥ ብዙ ተከታዮች እንዳሏቸዉና ብዙ የሠራዊቱ አባላት አመቺ ግዜ ባገኙ ቁጥር ከነትጥቃቸዉ ወገንን ነፃ ከሚያወጣዉ ጦር ጋር ለመቀላቀል ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸዉን ገልፀዋል።

በሌላ በኩል በተለይ ወጣቶችን በተመለከተ ደግሞ በቅርቡ ቀንና ማታ የሚከታተላቸዉን የወያኔ የስለላ መረብ በጣጥሰዉ ወደ ጎረቤት አገር የተሰደዱት የአማራ ክልል ወጣቶች ማህበር ፕሬዚዳንት ወጣት ዘመነ ካሴና የአባይ ፍሬዎች ወጣቶች ማህበር ሊ/መንበር የነበረዉ ወጣት ከፍያለዉ ጌጡ ጉዳይ የወያኔ ስርዐት ከማይወጣዉ አዘቅት ዉስጥ የወደቀ መሆኑን የሚያሳይ ጉልህ ማስረጃ ነዉ ሲሉ ብዙዎች ያለጥርጥር በመናገር ላይ ይገኛሉ። "ብአዴን" ማለት አማርኛ ተናጋሪ የህወሀት ክንፍ ነዉ፤ የብአዴን ባለስልጣኖች "እስከዛሬ በስማችን ስትቀልዱ ኖራችኋል ከእንገዲህ ወዲያ ግን ይበቃችኋል" ብለዉ አምርረዉ የተናገሩት ሁለቱ ወጣት መሪዎች ከአሁን በኋላ እስከመረሻዉ ታግለን የወያኔን ዘረኞች ከማሰወገድ ዉጭ ሌላ ምንም አመራጭ የለም ብለዉ መናገራቸዉ ወያኔ በሁሉም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ዉስጥ የተጠላ መሆኑን በግልጽ ከማሳየቱም በላይ ይህ ስርዐት በዚህ መልኩ በፍጹም ሊቀጥል አንደማይችል የኢትዮጵያን ጉደይ የሚከታተሉ ሁሉ የሚስማሙበት ጉዳይ ሆኗል።

## የወያኔ ባለስልጣናት ቤተሰቦቻቸውንና ገንዘብ ወደ ውጪ ሀገር ማሸሽ መጀመራቸውን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ

የቀድሞው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰራተኛ አቶ ሙሉነህ ዮሃንስ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚሰሩ ምንጮችን ጠቅሰው ይፋ እንዳደረጉት በሚኒስትር ደኤታ ማእረግ እየተጠራ እውነተኛው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትርና የሀይለማርያም ደሳለኝ አለቃ የሆነው አምባሳደር ብርሃነ ገብረክርስቶስ በርካታ ገንዘብ ይዞ ወደ ብራስልስ ቤልጂየም ከተጓዘና በመለስ አስታማሚነት ከከረመ በኋላ ሰሞኑን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ እየተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል። ብርሃነ ምናልባትም በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ደርሶ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ሌላው የመለስ ዜናዊ የደህንነት ሹም በመሆን ለረጅም ዓመታት ያገለገለውና በአሁኑ ወቅት በጣሊያን አምባሳደር ሆኖ እየሰራ የሚገኘው አምባሳደር ሙሉጌታ ዓለምሰገድ ዩኒቨርሲቲ ትማር የነበረች ልጁን ትምህርቷን እንድታቋርጥ ማድረግ ጭምር በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ መላ የቤተሰቡን አባላት ወደ ጣልያን ማሸሹ ተረጋግጣል።

ከዚህም ሌላ ከኢሳት ጋዜጠኛ አበበ ገላው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ተልእኳችሁን አልተወጣችሁም በሚል ወደ ሀገር ቤት ከተጠሩት ተበጀ በርሄ፣ ተስፋዬ ይልማ፣ ሙሴ ታረቀኝ እና አልማዝ አምሃ ከተባሉት በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የዘርፍ ሀላፊዎች መካከል ለጊዜው አልማዝ ብቻ የተመለሰች ሲሆን እሷም ብትሆን ቤተሰቦቿን እዛው አሜሪካን ትታ መመለሷ ተሰምቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌሎች የስርዓቱ ባለስልጣናት በበኩላቸው በርካታ ገንዘብ በወያኔ ወታደሮች በማሳጀብ ወደ ኬንያ እያሸሹ መሆናቸውን በኬንያ ካሉ የኤምባሲ ምንጮች መረጃ ማግኘታቸውን አቶ ሙሉነህ ገልጸዋል።

እንደ ምንጮቹ መረጃ ገንዘቡን በአውሮፕላን ማጓጓዝ ያልተፈለገው ትኩረት እንዳይስብ ለማድረግ ሲሆን በየብስ በቀላሉ ሸቀጥ በማስመሰል በወያኔ ወታደሮች አሳጅቦ ድንበር ማሻገር በመቻሉ ነው። እናም ይህ ሽሽትና ዝርፊያ ስርዓቱ እየተፍረከረከ ወደማይቀረው ሞቱ እየተቃረበ መምጣቱን አመላካች ነው።

## የኢትዮጵያ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት አባላትን ያቀፈው ነጻ የኢትዮጵያ ሰራዊት ንቅናቄ ለአንድነት፣ ለፍትህ፣ ለነጻነት ( ነኢሰን ) . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለውጦች እንዲመጡ የድርሻውን ተወጥቷል በማለት ያስታወሰው መግለጫው ዛሬም በሀገራችን በነጻነት ፋንታ ባርነት፣ በእኩልነት ፋንታ ዘረኝነት፣ በዴሞክራሲ ፋንታ አፈና ነግሶ ህዝብ መራራ ህይወት እየገፋ ስለሚገኝ፣ ይህ አስከፊ ሁኔታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲወገድ ህዝቡ ከሚያደርገውን ትግል ጎን ለመሰለፍ የመከላከያ ሰራዊት ሃይል ለዓመታት በህቡእ ሲደራጅ ቆይቶ " ነኢሳን " እውን በማድረግ ለተግባር እንቅስቃሴ ዝግጁ ሆኗል ብሏል።

መግለጫው በማከልም በዚህ አሳሳቢና ወሳኝ ወቅት የሀገሪቱን ህልውና አስከብሮ፣ ህዝቡን ከእርስ በእርስ እልቂት ለማዳንና ኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራሲያዊ ባህልና ዘመን እንድትሸጋገር ለማድረግ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በመደራጀት እያካሄደ ያለውን ትግል ለመቀላቀል ተዘጋጅቷል በማለት አስገንዝቧል።

አያይዞም የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ የህዝብ አገልጋይ እንጂ የአምባገነኖች ሃብት ማከማቺያና የስልጣን ጥም ማርኪያ መሳሪያ እንደማይሆን በመግለጽ፣ ይህ እምነቱ በወታደርነት ሲመለመል ለህዝብ የገባው ቃልኪዳን መሆኑንና የዛሬውም የትግል አንድነት ውሳኔ የዚሁ ቃልኪዳኑ ተሃድሶ መሆኑን አብራርቷል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔን ለማስወገድ በምድር ላይ ለሚደረገው ትግል አስተዋጾ ለማድረግ እራሳቸውን አድራጅተው የሚመጡት ሃይል ሁሉ ትግላቸው በህዝብ ምርጫ ብቻ ስልጣን የሚያዝበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት እስከሆነ ድረስ አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ሲገልጽ መቆየቱ ይታወሳል። '

የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የአገራቸውና የልጆቻቸው የወደፊት ዕጣ የሚያሳስባቸው በወያኔ ሰራዊት ውስጥ ያሉ የህዝብ ልጆች ሁሉ ለፍትህ ለእኩልነትና ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ለማገዝ ዛሬውኑ ከህዝብ ጎን እንዲሰለፉ የንቅናቄውን ጥሪ በዚህ አጋጣሚ ማስተላለፍ ይወዳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org